# የመድረክ የተቃውሞ ሰልፍና መፈክሮቹ

## ክፍል ሁለት

አዲስ ቶልቻ

12-18-14

“የመድረክ የተቃውሞ ሰልፍና መፈክሮቹ” በሚል ርዕስ በቀረበው ክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ መድረክ በቅርቡ ያካሄደው ሰልፍ ላይ የታዩ በጎ ነገሮችን አንስተን፣ በሌላ በኩል በሰልፉ ላይ መሰረተ ቢስ መልዕክቶች መተላለፋቸውን በማስታወስ ከእነዚህ መሃከል “ከምርጫው በፊት የምርጫ ሜዳው የሚስተካከልበት ውይይትና ድርድር እንዲካሄድ እንጠይቃለን” በሚል የተስተጋባውን መፈክር ይዘት ተመልክተን ነበር ያበቃነው። በዚህ ክፍል ሁለት ፅሁፍ ደግሞ “የኑሮ ውድነቱና የተጎሳቆለው የህዝባችን ህይወት የኢህአዴግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲ ወጤቶች ናቸው” በሚል በተቃውሞ ሰለፉ ላይ የተስተጋባውን መልዕክት እንመለከታለን።

እርግጥ ነው መድረክ ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ የተለየ የኢኮኖሚና መህበራዊ ልማት ፖሊሲ የመያዝ ሕገመንግስታዊ መብት አለው። ይህን ፖሊሲውን በአማራጭነት አቅርቦ በምርጫ ላይ የመወዳደር መብትም አለው። የመድረከ አመራሮች መድረክን ወክለው እንዲሁም በሌሎች ፓርቲዎች ተወካይነት ከዚህ ቀደም ምርጫ ላይ ተወዳድረው ያውቃሉ። በሕዝብ ውክልናም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ለመሆን የበቁም ነበሩ። መደረከ የኢህአዴግን ፖሊሲዎች የመተቸት መብትም አለው። ትችቱ ግን በተጨባጭ ማስረጃና አመክኗዊ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል። ከትችቱ ጋር አያይዞ ቢመረጥ ተግባራዊ የሚያደረገውን ግልፅ አማራጭም ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ከዚህ ውጭ ካለምንም ተጨባጭ ማስረጃ መቃወምና ማጥላላት ተገቢ አየደለም። የፖለቲካ ባህል እድገቱንም ያቀነጭረዋል። የመድረክ አመራሮች መሰረተ ቢስ ተቃውሞና ትችት በመሰንር ይታወቃሉ። ሰሞኑን የፓርቲው (የመድረክ) ሊቀመንበር ሆነው የተሰየሙት ፕ/ር

በየነ ጴጥሮስ ከሶስት አመት በፊት እርሳቸው የተካኑበትን የሰነህይወት  ሳይንስ እንኳን ባላገናዘበ ሁኔታ “በሃገሪቱ በተከሰተ ቸነፈር ምክንያት ሰዎች ሳርና አረም እየተመገቡ ለመኖር የተገደዱበተ ሁኔታ ተፈጥሯል” በለው እንዳወሩት አይነት ፀያፍ ውሸት በመቀባጠር የኢህአዴግን ፖሊሲና የፖሊሲ አፈፃፀም ለማጣጣል መሞከር ለህዝቡም ለሃገሪቱም የማይጠቅም ከአጭበርባሪነት ያልተለየ አካሄደ ነው።

ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ “ሰዎች ሳርና አረም እየበሉ ነው” በለው በእርሳቸው እደሜ ካለና የባለፉ ዓመታት የፖለቲካ ተሳተፏቸው አኳያ የማይጠበቅ ውሸት ባወሩበት ሰሞን ምስራቅ አፍሪካ ባለፉ አራት አስርት አመታት ከተከሰቱ ሁሉ አስከፊ በተባለ ድርቅ ተመትቶ አስከፊ ቸነፈር ገብቶ ነበር። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ይህን ድርቅ ያስከተለውን የምግብ እጥረት የውጭ እርዳታ ሳይደርስላት በራሷ የመጠባበቂያ ይእህል ክምችት መቋቋም ችላ ነበር። ፕ/ር በየነ ይህን በኢተዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ የታየ ድርቅ የሚያስከተለውን ረሃብ የመቋቋም አቅም ለማጣጣል ነበር ወሸት የፈጠሩት።

ያም ሆነ ይህ የመደረክ አመራሮች  ከላይ እነደተጠቀሰው አይነት የመንግስትንና የገዢውን ፓርቲ በጎ ተግባራት የሚያጎላ አቢይ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ አለያም መንግስት ላይ መረር ያለ ትችት በመሰንዘር በውጭ ሃገር የሚገኙ በጭፍን ጥላቻ የታወሩ የተምታታባቸው ተቃዋሚዎችን ማረከው የገንዘብ ድጋፍ ማገኘት ሲያሰኛቸው ድንገት ከእንቅልፋቸው ባነው “ኢኮኖሚው አላደገም፣ ሕንፃና መንገድ ብቻ ነው የተገነባው፣ ምንትስ ቅብጥርስ” በሚል ከሚቀባጥሩት ያለፈ መሬት የረገጠ ትችትና አማራጭ አቅርበው አያውቁም።

አመራሮቹ የየግል ህይወታቸውን ለማቃናት በውጭ ሃገራት ለአመትና ለወራት ቆይተው አሁን ምርጫ ሲደርስ ተሰባሰበው ዳግም ተመራርጠው ነው “ ድህነት፣ የኑሮ ውድነት . . .” የሚል ስለሃገሪቱ ምንም እንደማያወቁ የሚያሳብቅባቸውን ወሬ ያወሩት። እውነቱን ለመናገር መድረክ ምን አይነት ፓርቲ እንደሆነ - ምን አይነት የፖለቲካ መርህ እነደሚያራምድ፣ ምን አይነት አማራጭ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎች እንዳሉት አንድም ኢትዮጵያዊ አያውቅም። ያላወቁት ሰላልገባቸው ወይም ችላ ሰላሉ ሳይሆን ፓርቲው በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ተናግሮ ስለማያውቅ።

ኢሀአዴገ ግን የሚከተለውን ከማንም ያለተኮረጀ ወይም ማንንም ለማስደሰት ሳይሆን "በኢትዮጵያ ልክ የተዘጋጀ ነው" ያለውን የፖለቲካል ኢኮኖሚ ምርህ፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎች ሳያሰልስ በግልፅ ለህዝብ እያሳወቀ ይገኛል። እርግጥ ይህን እነዲያደርግ ያደረገው በውክልና ስልጣን ስለወሰደና ስልጣን ላይ በሚቆይባቸው ግዜዎች ውስጥ፣ ፖሊሲዎቹ ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ የመንግስት ህግ ሆነው ሰለሚወጡ ህግና ደንብን የማስተዋወቅ ስራ መስራት ሰላለበት ሊሆን ይችላል ሳያሰልስ እንዲያሳውቅ፣ ህዘቡም እንዲያወቀው ያደረገው።

መደረክም ሆኑ ሌሎች ተቃዋሚዎች ገሚሶቹ መኖራቸው እሰኪረሳ አመራሮቻቸው ከሃገር ወጥተው ፀጥ እረጭ ብለው በመቆየታቸው፣ የተቀሩትም በሃሰተኛ ወሬ ውዥንብር በመንዛትና "የተቋወሞ ሰልፍ፣ የድጋፍ ፊርማ፣ የሚሊየኖች ድምፅ ምንትስ . . ." እያሉ በመንበዛበዝ አቋማቸውን የመግለፅና የማራመድ መብታቸውን ፖሊሲዎቻቸውንና የፖለቲካል ኢኮኖሚ መርሃቸውን ለማሳወቅ ሊጠቀሙበት ይችሉ የነበረበትን ግዜና ዕድል በከንቱ ማባከናቸውን ታዝበናል።

ኢሀአዴግ ፖሊሲዎቹን አሰማምሮ በማሰተዋወቅ በቻ አልለተገደበም። አሳመሮ ተገባራዊ አደረጓቸዋል። ኢሀአዴግ ተግባራዊ ባደረገው የልማት ፖሊሲ ምክንያት ባለፉ አስራ ሁለት ዓመታት በሃገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ባለሁለት አሃዝ ተከታታይ እድገት ማሰመዘገብ ተቸሏል። ይህ ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮሚ እድገት  ኢሀአዴግ የሚከተለው "ልማታዊ ዴሞክራሲ" የፖሎቲካል ኢኮኖሚ መርህ በሚጎመዝዛቸው መንግስታትና ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት ጭምር ተቀባይነተ አግኝቷል።

የዓለም ባንክና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት፣ ሌሎችም ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት የእድገቱን ትክክለኛነት በራሳቸው መንገድ ፈትሸው ተቀበለዋል። ምንም ጥናት ያላደረጉትና ሃገሪቱንና የፖለቲካ ስራቸውን ጣጥለው በውጭ ሃገራት በግል ጉዳያቸው ተጠምደው የከረሙት  የመድረከ አመራሮቸ ብቻ ናቸው እድገቱ ያልታያቸው፤ ወይም መቀበሉ የጎመዘዛቸው።

የባለፉት አስራሁለት ዓመታት ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ እድገት በህዝቡ ህይወት መሻሻል የተገለፀ ተጨባጭ ልማት ለመሆን የበቃ ነው። የህዝቡን ኑሮ በማሻሻል ረገድ ከጥቂት አመታት በፊት ከ50 በመቶ በላይ የነበረውን የድህነት መጠን ከ29 በመቶ በታች ማወረድ አስችሏል። ኢትዮጵያ አሁን በሃገር አቀፍ ደረጃ በምግብ ራስዋን የቻለች ሃገር ለመሆን በቅታለች። በአመት የሚመረተው 300 ሚሊየን ኩንታል የእህል ምርት ከህዝቡ ቁጥር አኳያ ሲመዘን ሁሉንም ዜጎቹ መመገብ የሚያስችል ነው። ሃገሪቱ በምግብ ራሳን የመቻሏ ሰኬት በቅርቡ በዓለም የምግብ ድርጅት እውቅና ተሰጥቶታል። ለዛውም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ በምግብ ራስን መቻልን አስመልክቶ በሚሊኒየም የልማት ግብ ያስቀመጠው የግዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አሰቀድማ ኢተዮጵያ እቅዱን ማሳካት በመቻልዋ ነው እውቅና የተሰጣት።

አሁን ባለው ሁኔታ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ፍላጎትን ማማሏት ባይቻልም፣ የሀገሪቱን አጠቃላይ የምግብ ፍላጎት ግን ማሟላት ተችሏል። የግብርናን ምርታማነት የማሳደጉ ስራ ቀጣይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም ዜጎች በምርት ስራ ላይ እነዲሰማሩና ገቢ እነዲኖራቸው በማድረግ በቤተሰብ ደረጃ ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል።

ኢትዮጵያ አሁን አስከፊ ድርቅ እንኳን ቢከሰት ዜጎቿ እነደ ከዚህ ቀደሙ በቸነፈር እንዳይረግፉ ማድረግ የሚቻለበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። ከሶስት ዓመት በፊት በ1966 እና 1976/77 ተከሰቶ ለአሰከፊ ቸነፈር ምክንያት ሆኖ ከነበረው የባሰ ድርቅ ተከሰቶ የነበረ ቢሆንም፣ ድረቁ ያስከተለው የምግብ እጥረት እልቂት ወዳስከተለ ረሃብነት ሳይቀየር መከላከል መቻሉ ለዚህ አስረጂነት ሊጠቀስ ይችላል። ይህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እና ዓለም የሚያውቀው እውነት ነው።

የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ተከታታይ እድገት ማሳየቱ በሌሎችም እውነታዎቸ ተገልጿል። ሃገሪቱ አሁን በራሷ አቅም - በህዝብና በመንግስት ርብርብ እያከናወነች ያለችው 80 ቢሊየን ብር ገደማ ወጪ የሚጠየቀው ታላቁ የኢተዮጲያ ህዳሴ ግድበ ግንባታም የሃገሪቱ እድገት ማሳያ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በቅረቡ ሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ለውጭ ገበያ ያቀረበችው ቦንድም የሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ውጤት ነው። ሃገሪቱ ከበለፀጉ ሃገራት ጋር ያላት

ግንኙነት ከእርዳታ ጠያቂነትና ለጋሽነተ ወጥቶ ወደንግድ ሽሪክነት መሸጋገሯን የሚያሳይ ተጨባጭ ምስክር ነው። ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የ2 ቢሊየን ዶላር ቦንድ የመሸጥ አቅም እንዳላት ተረጋግጧል። በቅረቡ 1 ቢሊየን ዶላር ቦንድ ለሽያጭ አቅርባ የቀረበው የግዢ ጥያቄ ግን ከ2 ነጥብ 6 ቢሊየን ዶላር በላይ እንደነበረ የታወሳል።

በኢህአዴግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ስኬት ዙሪያ በርካታ ተጨባጭ ማስረጃዎችን መዘረዘር ቢቻልም፣ ከላይ በተገለፁት በቀላሉ የሚታዩና ዓለም የመሰከረላቸውን ብቻ ጠቅሼ ወደ ሌላ ጉዳይ ልሸጋገር።

መድረክ የኑሮ ውደነትንም የሚመለከት ጉዳይ አንስቷል፤ በተቃውሞ ሰለፉ ላይ ባስተጋባው መልዕክት። እርግጥ ነው የኢኮኖሚ እደገቱ ጎልቶ መውጣቱን ተከትሎ በተለይ ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ የዋጋ ማሻቀበ ተከሰቷል። የዋጋ ማሻቀቡ፣ የኢኮኖሚ እድገቱ የገበያ ፍላጎት በፍጠነት እንዲያድግ ያደረገ በመሆኑ የተከሰተ ነው። በመሆኑም እነደቺኮኖሚ ቀውስ የሚታይ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ትላልቅ ፕሮጀከቶችን በራስ አቅም ለማከናወን (ለአብነት ያህል ያለምንም የውጭ ብድርና እርዳታ የተከናወኑትን የተከዜ የሃይል ማመንጫ ግድብና የጣና በለስ የሃይል ማመንጫ የመሳሰሉትን) ለማከናወን የተከተለው የገንዘብ ፖሊሲ የዋጋ ንረቱን ጠንከር እነዲል አስተዋፅኦ ማድረጉን መንግስት ማሳወቁ የታወሳል። ባለፉ ዓመታት የበለፀጉ ሃገራትን የመታው የኢኮኖሚ ቀውስና የነዳጅ ዋጋ መጨመርም የዋጋ ነረቱን የማባባስ አሰተዋፅኦ ነበራቸው።

መንግስት የዋጋ ንረቱ መከሰት እነደጀመረ ምክንያቶቹን ነበረ ያጠናው። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የኢኮኖሚ እደገቱ አንዱ የዋጋ ንረቱ ምክንያት ነበር። የኢኮኖሚ እደገቱ ያስከተለውን የዋጋ ንረት የቀጥላል በሚል ግምት ገበያውን በሞኖፖል የተቆጣጠሩ ነጋዴዎች የፈጠሩት ሰውሰራሽ የገበያ ንረትም በምክንያትነት ተወስዷል። ሌላው መንግስት የትላልቅ ፕሮጀክቶችን ወጪ ለመሸፈን ከብሄራዊ ባንክ ገንዘብ መበደሩ የፈጠረው ነው።

የዋጋ ንረቱ መንስኤዎቸ እነደተለዩ የኢኮኖሚ እደረገቱ የፈጠረውን ጫና ለመቋቋም የዋጋ ንረቱ ዋነኛ ተጎጂ ለሆኑ የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ማሻሻያ ተደረገ። የነጋዴውን ሰው

ሰራሽ የዋጋ ንረት ለመከላከል ደግሞ መሰረታዊ በሆኑ ሸቀጦች፤ የምግብ ዘይት፣ ስኳር፣ ዳቦና የስንዴ ዱቄት ላይ የስርጭትና የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግበት ስርአት ተዘረጋ። መንግስት ሲከተለው የነበረውን ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ የመበደር አካሄድ በማሻሻል ገንዘብ መበደር ካስፈለገው በኢኮኖሚ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ካለ ገንዘብ ብቻ ለመበደር ወስኖ ተግባራዊ በማድረግም የዋጋ ነረቱነ የሚከላከል የመፍትሄ እርምጃ ወስዷል። እነዚህ የኢህአዴግ የፖሊሲ እርምጃዎች ናቸው።

ይህን ተከተሎ "የዋጋ ንረቱን ማስተካከል ይከብዳቹሃል" ሲሉ የነበሩ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትን ጭምር ባስገረመ ሁኔታ ከ40 በመቶ በላይ ደረሶ የነበረው የዋጋ ንረት ወደአንድ አሃዝ ወረደ። ይህ ከሆነ አሁን ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል። የባለፈው ወር፤ ማለትም የህዳር ወር የዋጋ ንረት መጠነ 5 ነጥብ 9 በመቶ ነበር።

አሁን በሃገሪቱ የዋጋ ንረት ችግር የለም። ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር የሚሻሻል ነባር ችግር የፈጠረው የኑሮ ጫና አሁንም መኖሩ ባይካድም በመንግስት ፖሊሲ ሳቢያ በተከሰተ የዋጋ ንረት በመነሳቆል ላይ ያለ ዜጋ የለም ማለት ይቻላል። አናም መደረክ ዋሸቶናል። እርግጥ አመራሮቹ ውጭ ሃገር የራሳቸውን ስራ በማከናወን ተጠምደው በመቆየታቸው ከሶስት ዓመታት በፊት ተከሰቶ የነበረው የዋጋ ንረት በአስደናቂ ሁኔታ መሻሻሉን አልሰሙ ሊሆን ይችላል። ይህም ቢሆን ያልሰሙትንና የማያወቁትን ጉዳይ የፖለቲካ አጀንዳ አድረጎ ማቅረብ ከፖለቲካ ስነምግባር አንፃር ፀያፍ ነው።

በአጠቃላይ መድረክ ህግና ስርአት አክበሮ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ያሳየው ፍላጎትና ተነሳሽነት "አበጀህ" የሚያሰኝ፣ አጉራ ዘለል ፓርቲዎችን የሚያስተምርና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ባህልን በማዳበር ረገድ አስተዋፅኦ ሊኖረው የሚችል በመሆኑ በበጎ ጎን የሚታይ ነው። ይህን ህገመንግስታዊ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቋምን የማስተላለፍ መብት ትክክለኛ ያልሆኑ ውዥንብር ፈጫሪ አቋሞችንና አጀንዳዎችን በማስተጋባት ያለአግባብ መጠቀም ግን ሊታረም የሚገባው፣ ምናልባትም ከቅንነት ያልመነጨ ነው ተብሎ የገመታል። ሕገመንግስታዊ መብቶችን በአግባቡ መጠቀም ለሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አሰፈላጊ መሆኑን ሁሉም ወገን ሊያስታውስ ይገባል።